# አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ኢትዮጵያዊነትን ለምን ፈለጉት?

ከ ንስረ ኢትዮጵያ (nisreethiopia@yahoo.com)

ተስፋዬ ገብረ አብ በደራሲነት ሙያ መተዳደር ከጀመሩ ሰንብተዋል:: ከሙያ በላቀ መልኩ መተዳደሪያነቱን አጥብቀው በመያዛቸው ቢመችም ባይመችም የተለያዩ ፅሑፎች ወይም መጽሓፍት አበርክተዋል ብልጥ የግዜውን ሁኔታ የሚያዩ ጎበዝም ናቸው::

ሙያ ሲያከብሩት ያከብራል:: ሽቀጥ ሲሆንና ዋጋ ካላገኘ ወይም የረከሰ ግዜ ያከስራል:: ሓቅ ሲያጥረው ደግሞ ያዋርዳል::

ብዙ ኢትዮጵያውያን ምነው እኚህ ሰው ብዙ ተናገሩ ብሎ የጠየቀበት ግዜ እሩቅ አይደለም በዛው በቡርቃ መፅሓፋቸው መዘዝ ደማቸው ደመ ከልብ የሆኑ ንፁሐን ኢትዮጵያውያንም እናዳሉ የሚናገሩ አሉ:: ቡርቃ የተንቆረቆረውን ያህል አልሸረሸረንም፤ ዉኃውም ታዝቦ ዝም ብሎአል፤ ግን ግን ይህ ህዝብ ይህን ያህል ዝምታ ለምን መረጠ?

ዕውን ደራሲው ህብረተሰቡን በአግባቡ ያውቁት ይሆን? እያለ ህዝቡ ለመጠየቅ በሚንደረደርበት ሁኔታ ውስጥ እያለ ቡርቃ ዝም ማለቱ ትምህርት ያልሰጣቸውና መማር ያቃታቸው እኚህ ግለሰብ አሁን ደግሞ ማስታወሻ በማስታወሻ አደረጉን::

ምስጋና እናቀርባለን::

ግን አንድ ትክክል የሚታይ ነገር አለ መጋለጥ ያለባቸው ግለሰቦች ተጋልጠዋል መዋረድ ያለባቸውም እንዲሁ ብዙም ባይሆን ተዋርደዋል ግን የኤርትራ እና የሻዕቢያ ቅኝት ያላቸው ግለሰቦች ሚስጥር ለደራሲውም ሚስጥር ሆነባቸውና ለአብዛኛዎቻችንም ሚስጢር አደረጉት:: ለነገሩ በርካታ ወገኖች ሳይነገራቸው ለካ ገብቷቸው ነበር:: የሻዕቢያ የረጅም ግዜ እቅድ ምን እንደሆነ ለመናገር ያልደፈሩት ስለማያውቁት ነው ብለን ተቀብለናል:: ግን እሳቸው አምነው ያልተቀበሉት ይመስላልና አንድአንድ አገር ወዳዶች እኚህ ግለሰብ በጦር ያልፈቱትን ህዝብ በብዕር ሊፈቱት ፈልገው ነው ብለው ማማት ጀምረዋል:: ሃሜት ጥሩ ባይሆንም::

ደራሲ ብልህ ነው፣ ደራሲ ቆራጥ ነው፣ ደራሲ እውነተኛ ነው፣ ደራሲ ሙሉ ልብ አለው፣ አሁን ግን ግማሽ መረጃ በግማሽ ልብ የሚጽፉ መሰሪ ደራሲያን ለምን በደራሲያን ስም ተቀፈቀፉ?

ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ህዝብ አንበርክኳል ለማለት አልደፈሩም እንጂ የተቻላቸውን ያህል የሻዕቢያን ኃያልነት ሊነግሩን ዳድተዋል:: የቅኝ ገዥዎችን አከርካሪ የሰበረ ኢትዮጵያዊ በባንዳ መንጋ እየተነዳ ነው እስኪሉን እየጠበቅን ከሆነ በጣም የዋህነት ነው::

እኚህ ሰው መለስን በአግባቡ ለመግለፅ ለምን ተቸገሩ:: ወያኔ ያለ መለስ ወያኔነቱ እንዴት ትርጉም ይኖረዋል? መለስ በኢትዮጵያ ላይ ያሳለፋቸውና ያደረሳቸው ጥፋቶች ደራሲው ከፃፉትና እውነት ነው ብለው ከነገሩን ከተራሮቹ በላይ የህዝብን ሐቅና ኢትዮጵያዊነትን ለማውደም ቆርጦ መነሳቱ እንዴት ተደበቀባቸው? እውን የመለስ ዜናዊ ድብቅና የረጅም ግዜ የባንዳነት ተልዕኮ ለእኚህ ግለሰብ አልገባቸው ይሆን?

ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚስማማበት በግማሹም ቢሆን ለነሱ ያልተመቿቸውን ወያኔዎች እንድናውቃቸው አድርገዋል፤ ግን አሁንም ለኛ ያልተመቹን ኃይሎች ተሸሞንሙነው ቁጭ ብለዋል:: ምክንያቱም ደራሲው ስለዚህ ጉዳይ አላውቅም የሚል አቋራጭ ምላሽ ታጥቀው

የዘመቱ ናቸው:: እኛም በግድ እንዲጫወቱ አናደርግም:: የአራዳ ልጅ ደግሞ አስገድዶ አያጫውትም በቃ እሳቸውም በጨዋታው አይገደዱም::

ደራሲው ኢትዮጵያዊ ነኝ ብለው ብዙ ግዜ ነግረውናል:: እኛም አልገባንም እሳቸውም ማስረዳታቸውን አላቆሙም:: ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ቢሸፍቱና ኢትዮጵያን አፍ መክፈቻ ካደረጓቸው ሰነበቱ:: ግን ኢትዮጵያዊነት በንግግር ብቻ ነው እንዴ? ልባቸው የት እንዳለ እኛም እሳቸውም እያወቅነው በኢትዮጵያ ላይ ደፍረው አካፋውን አካፋ ለማለት ዳር ዳሩን የሚሽከረከሩት ምንአልባት ስለራሳቸው በማስታወሻ ጽሑፋቸው ያልነገሩን በረሃ ውስጥ የገቡት ቃል ኪዳን አላላውስ ብሏቸው ይሆን? ለመሆኑ ይህ ለምን ሆነ ብለው የሚጠይቁ ኢትዮጵያውያን መብዛታቸውን ታዝበው ይሆን? ይህን ጥያቄ ኢትዮጵያዊው ሁሉ በራሱ የመለሰው ነው:: ለጥቂቶቻችን ግን ብዥታ ፈጥሮብን የሳቸው ፓስፖርት የት እንደሆነ መለየት አቅቶን ግርታ ውስጥ እንገኛለን::

ለነገሩ ለእኛ ነው እንጂ ደቡብ አፍሪካ ለሚገኙና ኤርትራዊ ናችሁ ተብለው ለተፈረጁት ስደተኞች ግልጽ ነው:: አንዳንዴ የዕረፍት ግዜያቸውን ያሳልፋሉ:: ከተገኘ ከኢትዮጵያ በቀጥታ የሚገባውን አወዳይ ተንተርሰው፤ ካልሆነም ሻይ ቡና እያሉ:: እና ለእነዚህ ስደተኞች እሳቸው የሚነግሯቸውን የሰማን ኢትዮጵያውያን ነገሩ ሁሉ እኚህ ደራሲ ለእኛ በአደባባይ ከሚነግሩን ጋር ተቀላቅሎብን ግራ ገብቶናል:: አዎ ኤርትራዊ ናችሁ ለተባሉት ወገኖች የኢትዮጵያን ብሔሮች እያዋረዱ ይውላሉ:: ወያኔ የነገራቸውን ከሻዕቢያ ተልዕኮ ጋር በማጠናከር የረከሱ ስድቦችንና የሚያዋርዱ ቃላቶችን እያዘነበቡባቸው ነው:: አዎ እያዘነቡብን ነው::

እኚህን ግለሰብ እንደው ይህ ነገር ሃሜት ነው? ወይስ ሰዉ መቼም እውነት ሳያዝ አያወራም ብለን ከጠየቅን ከዘረኛው ወያኔ ስር ሊሽጉጡን ትግል ይገጥማሉ::

አሁን ደግሞ ኢላማቸው ስዬ አብርሃ ላይ ነው:: ለምን? ብለን ጠይቀን ይሆን? አዎ ይህን ጉዳይ ለምን እንደሆነ ወያኔም ሻዕቢያም እሳቸውም በደንብ ያወቁታል:: አቶ ስዬ ያፈሰሱትን ንጹህ የኢትዮጵያውያን ደም ከመናገር ወይም የኢትዮጵያን አንድነት ለማፍረስ ከቆፈሩት ጉድጓድ በላይ የስዬ የዚህ ሰሞን ሉዓላዊነት አቋም ለእኚህ ሰውና በጣት ለሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ጠላቶች ከፍተኛ ስጋት ሆኗል::

እንደውም ሃሜት እንዳይሆን እንጂ የሻዕቢያና የእኚህ ግለሰብ በመሃል አገሩ ላይ ያለው ጥላቻ ለወያኔ ካላቸው ጥላቻ ሳይብስ አይቀርም:: የ1997ቱ የቅንጅት ንቅናቄ ወያኔን ካስደነገጠው በላይ ለሻዕቢያና ለእኚህ ግለሰብ አደጋ ሆኖ ታይቶ እንደ ነበር የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ጥቂት አይባሉም::

እውን እኚህ ግለሰብ በኢትዮጵያዊነት የሚያምኑ ከሆነ የባህር በር አስፈላጊነት ለምን አልታይ አላቸው? ስለ ኢትዮጵያ የባህር በር ታሪክ ከባጫ ደበሌ ዳንስ ታሪክ በላይ አያውቁት የሆን? የዚህ ጉዳይ ሲነሳ ላብ ላብ የሚላቸውስ ለምንድን ነው? በኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ከወያኔ በላይ ሊከራከሩና የሁለቱን ህዝቦች አንድነት ለማዜም ለምን ይመርጣሉ?
ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከልብ ልብ ሊለው የሚገባው ነገር ተከስቷል:: እኚህ ግለሰብ ወያኔ እያደረሰ ካለው የአገር መበታተን ስራ በላይ ደፋ ቀና እያሉ ነው:: የእኚህ ግለሰብ ዓላማ ምን እንደሆነ ያልተረዳን ካለን ግን አሁንም ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ::

በወያኔ መቃብር ላይ የሚመሰረተው ጠንካራ ኢትዮጵያዊ መንግስት ለሻዕቢያ እና መሰል ርዝራዥች አሁንም ትልቅ ስጋት እንደሆነ እየታየ ነው::

ብንቀበለውም ባንቀበለውም እኚህ ሰው የኢትዮጵያን ሞት ለማየት እንቅልፍ አጥተዋል::